6919 E. 10th Street፣ Building C፣ Suite 2፣ Indianapolis፣ IN 46219
Vaccinateindiana.org • 317-628-7116 • clinic@vaccinateindiana.org

ውድ የ[SCHOOL NAME] ቤተሰቦች፣

በ[CLINIC DATE] ከ[CLINIC TIME]፣ የ Indiana Immunization Coalition (IIC፣ ኢንዲያና የክትባት ጥምረት) ለተማሪዎች በትምህርት ቀን በ[LOCATION] የክትባት ክሊኒክን ለማስተናገድ በቦታው ይገኛል። ይህ ተማሪዎቻችሁ ወደኋላ የቀሩባቸውን ክትባቶች እንዲወስዱ እና ለሚቀጥለው የትምህርት ዘመን (የቅድመ መደበኛ፣ 5ኛ እና 11ኛ ክፍል ተማሪዎች) ለመዘጋጀት ክትባቱን አሁኑኑ እንዲወስዱ ከፈለጉ ይህ አስደናቂ ዕድል ነው። ይህ አማራጭ አገልግሎት ነው። ተማሪዎ እንዲሳተፍ የማይፈልጉ ከሆነ እባክዎ የኦንላይን ምዝገባውን አያጠናቅቁ።

በክሊኒኩ ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች ክሊኒኩ በሚካሄድበት ጊዜ የሚጠበቁ ሁሉንም በACIP የሚመከሩ ክትባቶች ይከተባሉ። ተማሪዎ ምን ዓይነት ክትባቶች እንደሚያስፈልጉት ለማወቅ IIC የተማሪዎን የክትባት ታሪክ ይመረምራል። ሊሰጡ የሚችሉ ክትባቶች ዲ.ቲ.ኤ.ፒ/ቲ.ዲ.ኤይ.ፒ፣ ሄፓታይተስ ኤ፣ ሄፓታይተስ ቢ፣ ኤች.አይ.ቢ፣ ኤች.ፒ.ቪ፣ ኢንፍሉዌንዛ፣ ኤም.ኤም.አር፣ ማጅራት ገትር፣ ፖሊዮ፣ ቫሪሴላ፣ ጉንፋን እና ኮቪድ-19 ያካትታሉ። ለልጅዎ ምን ዓይነት የበሽታ መከላከያዎች እንደሚመከሩ የበለጠ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ እባክዎ ለሕፃናት እና ጎልማሶች በCDC የሚመከር የክትባት መርሃግብርን ይመልከቱ።

*ለማንኛውም የተለየ የክትባት እምቢታ ቢያንስ ክሊኒክ ከመድረሱ 48 ሰዓታት በፊት ወደ clinic@vaccinateindiana.org ኢሜይል ይላኩ ወይም ወደ 317-628-7116 ይደውሉ።

ማሳሰቢያ፣ IIC ግልጽ የወላጅ ጥያቄ ሳይኖር የኮቪድ ተከታታይ ክትባቶችን አይጀምርም፣ ነገር ግን የኮቪድ ተከታታይ ክትባቶች ከተጀመሩ እናጠናቅቃለን። ልጅዎ ተከታታይ የኮቪድ ክትባቱን ከጀመሩ እና ተከታታዩን እንዲያጠናቅቁ ካልፈለጉ እባክዎ ከታቀደለት የክትባት ክሊኒክ 48 ሰዓታት ቀደም ብለው ወደ clinic@vaccinateindiana.org ኢሜይል ይላኩ።

IIC ሁሉንም ኢንሹራንስ (የንግድ፣ Medicaid እና Medicare) ይቀበላል፣ እንዲሁም የመድሳን ዋስትና ለሌላቸውም ክትባቶችን በነፃ ይሰጣል።

ተማሪዎ እዚህ በትምህርት ቤት በክትባት ክሊኒኩ ውስጥ እንዲሳተፍ ከፈለጉ፣ እባክዎን የኦንላይን የምዝገባ ቅጹን እዚህ ይሙሉ፦ https://patients.vaxcare.com/registration **Enrollment Code IN65942።** እባክዎን እስከ [DAY BEFORE CLINIC] ድረስ ይመዝገቡ እና ያጠናቀቁት የኦንላይን ምዝገባ ተማሪዎ በትምህርት ቀን ክትባቱን እንዲወስድ እንደተቀጠረለት ቀጠሮ ማረጋገጫ ያገለግላል። ቅጹን በሌላ ቋንቋ ከፈለጉ ወይም ምዝገባውን ለማጠናቀቅ እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎን ትምህርት ቤቱን በ[PHONE # OR EMAIL] ያግኙ።

ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎ የትምህርት ቤታችንን ነርስ፣ [NAME] በ[EMAIL] ወይም [PHONE] ያግኙ።

ተማሪዎ በ[CLINIC DATE] የክትባት ክሊኒክ መገኘት ካልቻለ እና/ወይም ለመከተብ ፍላጎት ያላቸው የቤተሰብ አባላት ካሉዎት፣ እባክዎን የማህበረሰብ ክሊኒክ የቀን መቁጠሪያን ለማየት የQR ኮድን ቅኝት ያድርጉ። ምንም ቀጠሮ ሳያስፈልግ ሁሉም ሰው ወደ እነዚያ የማህበረሰብ ክሊኒኮች መሄድ ይችላል።

እናመሰግናለን፣ [CONTACT NAME]